# ወልቂጤ ዩኒቨርሲቲ

## የማህበራዊ ሳይንስ እና ስነ-ሰብ ኮሌጅ

## የቴአትር ጥበባት ትምህርት ክፍል

## “የጋሞ ብሄረሰብ ሀገር በቀል የግጭት አፈታት ከትውፊታዊ ተውኔት አላባውያን አንጻር”


የጥናቱ አቅራቢ ተማሪ

የምስራች ስምኦን


ነሀሴ 2013 ዓ.ም

# “የጋሞ ብሄረሰብ ሀገር በቀል የግጭት አፈታት ከትውፊታዊ ተውኔት  አላባውያን አንጻር”


የጥናቱ አማካሪ

መምህር ዳንኤል በኩረ


በቴአትር ጥበባት ትምህርት ክፍል ባችለር ኦፍ አርትስ ድግሪ ማሟያነት የተሰራ

ነሀሴ 2013 ዓ.ም

## የአማካሪው ማረጋገጫ

ይህ ጥንታዊ ፅሁፍ በወልቂጤ ዩኒቨርስቲ የቴአተር ጥበባት ትምህርት ክፍል የመጀመሪያ ዲግሪ ማመከሪያመስፈርት መሰረት ድጋፍ የተደረገለት መሆኑን አረጋግጣለሁ።

የአማካሪው ስም..............................................ፊርማ.........

ይህ በተማሪ የምስራች ስምዖን "የ ጋሞ ብሄረሰብ ሀገር በቀል የግጭት አፈታት ከትውፊታዊ ተውኔት አላባዊያን አንጻር" በሚል ርዕስ የተሰራውን የመጀመሪያ ዲግሪ ማሚያ ጥንታዊ ፅሑፍ የዩኒቨርስቲውን ጥራት ደረጃ ያሟላ እና ለቴአተር ጥበባት ትምህርት ክፍል ተቀባይነት ያገኘ መሆኑን ማረጋገጫ ነው።ይህም በፈታኝ ኮሚቴ ተረጋግጣል።

ፈታኝ1 ፊርማ ፊርማ

............................................. .........

ፈታኝ2 ፊርማ

.............................................. ..........

ቀን----------------------

## ምስጋና

በቅድሚያ ለዚህ ላበቃኝ ለልዑል እግዚአብሄርን ላቅ ያለ ምስጋናዬን አቀርባለው፡፡ በመቀጠል ይህንን ሪሰርች እየተመለከተ ስህተቶችን በማረም እና ጠንካራ ጎኖችን በማዳበር ለጥናቱ መሪ ሀሳቦችን በመለገስ ያገዘኝን ለመምህር ዳንኤል በኩረ ከፍ ያለ ምስጋና አቀርባለው፡፡ ለጥናቴ አስፈላጊ የሆኑትን የጽሁፍ መረጃ በመስጠት ለተባበሩኝ የጋሞ ባህል እና ቱሪዝም ሰራተኞች ምስጋናዬ ላቅ ያለ ነው፡፡ ድጋፉን በመስጠት ይህንን ጥናት በጽሁፍ አገልግሎት ያገዘኝን ኤፍሬም ወንደሰንን ምስጋናዬ የላቀ ነው፡፡ በመጨረሻም ትምህርቴን ከጀመርኩበት ቀን አንስቶ አሁን እስካለሁበት ደረጃ ድረስ ላደረሱኝ ቤተሰቦቼ ለውድ እናቴ እና አባት ከፍ ያለ ምስጋናዬን አቀርባለሁ፡፡

# አበርክቶ

በአዲስ አበባ በቡራዩ ከተማ ለሞቱት እና ለተጎዱት ለጋሞ በሔረሰብ ይሁንለኝ።

# አጠቃሎ

ይህ ጥናታዊ ጹሁፍ የጋሞ ሃገር ሰብ ግጭት አፈታት ከሃገረሰባዊ ድራማ አላብዉያን አንጻር በሚል ርዕስ የቀረበ ነዉ።ጥናቱ የሚያቶክረዉ የጋሞን ግጭት አፈታት ምን እንደሚመስል ያሳየናል።እንዲሁም ሃገር በቀላዊ ምንነት ፣ ሀገር በቀላዊ ሙዚቃ ፣ ሃገረ በቀላዊ ዳንስ እንዳሉት ትተነትናለች። ጥናቱ በጋሞ ዞን ግጭት አፈታት የሚደረገዉን ለመተንተን ገላጭ የምርመር ዘዴን እንዲሁም ቃለመጥይቅ ምልከታ እንደመረጃ ማሰባሰቢያ ዘዴ ተጠቅማለች።

## ማውጫ


ምዕራፍ አንድ ....................................................................................................1

መግቢያ ....................................................................................................1

1.1. የጥናቱ ዳራ ....................................................................................................1

1.2. የጥናቱ ዓላማ ....................................................................................................2

1.2.1. ዋና ዓላማ ....................................................................................................2

1.2.2. ንዑስ ዓላማ ....................................................................................................2

1.3. የጥናቱ ጠቀሜታ ....................................................................................................2

1.3.1. ዋና ጠቀሜታ ....................................................................................................2

1.3.2. ንዑስ ጠቀሜታ ....................................................................................................2

1.4. የጥናቱ ወሰን ....................................................................................................2

1.5. የጥናቱ ዘዴ ....................................................................................................3

1.5.1. የመረጃ አሰባሰብ ዘዴ ....................................................................................................3

1.5.2. የመረጃ መተንተኛ ዘዴ እና የጥናቱ አይነት ....................................................................................................3

1.6. የጥናቱ አወቃቅር ....................................................................................................3

1.7. የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት ....................................................................................................4

1.8. ጥናቱ የሚያነሳቸው ጥያቄዎች ....................................................................................................4

1.9. በጥናቱ ወቅት ያጋጠሙ ችግሮች ....................................................................................................4

1.9.1. የተወሰዱ መፍትሄ ....................................................................................................4

ምዕራፍ ሁለት ....................................................................................................5

የተዛማጅ ጹሁፎች ቅኝት ....................................................................................................5

2.1. የተዛማጅ ጹሁፎች ቅኝት ....................................................................................................5

2.2. የሀገር በቀል ድራማ ምንነት ....................................................................................................5

ሀገር በቀል ትውን ጥበብ ....................................................................................................5

ሀገር በቀላዊ ድራማ ....................................................................................................6

ሀገር በቀላዊ ሙዚቃ ....................................................................................................7

ሀገር በቀላዊ ዳንስ ....................................................................................................8

ምራዕፍ ሶስት ....................................................................................................9

የመረጃዎች ትንታኔ ....................................................................................................9

3.1. የጋሞ መልካዓ ምድራዊ አቀማመጥ ....................................................................................................9

3.1.1. የጋሞ የግጭት አፈታት ስነ- ስርዓት ........ 11
3.1.2. የቱጌ የግጭት አፈታት ዘዴ........ 11
3.1.3. ዱቡሻ ጭማ ቴታ ........ 12
3.1.4. የግጭት መንስኤዎች ........ 12
3.1.5. ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ የግጭት መንስኤዎች ........ 13
3.1.6. ግጭቶችን የማርገብ ስራ የሚሰሩ ባህላዊ መሪዎች........ 14
3.1.7. የጋሞ የግጭት አፈታት ስርዓት ከሀገረሰብባዊ ድራማ አላባውያን አንጻር ምን ይመስላል ........ 15
3.1.8. ባህላዊ መሪዎች በግጭት አፈታት ላይ ያላቸው ሚና ........ 15
3.1.10 የጋሞ ሀገር በቀል ከግጭት አንጻር ........ 16
3.1.11 የጋሞ ሀገር በቀል ከሙቼት አንጻር........ 17
ምዕራፍ አራት ........ 18
4.1. ማጠቃለያ........ 18
4.2. የመፍትሄ ሀሳብ ........ 18
ታካይ ክፍል ........ 19
ዋቢ መጽሀፍት........ 20
አባሪዎች........ 21

# ምዕራፍ አንድ

## 1. መግቢያ

በኢትዮጵያ ሀገራችን ብዙ አይነት፣ ባህሎች፣ ወጎች ልማዶች እንዳለ መገመት አይከብድም፡፡ እነዚህን ጠብቆ ለማቆየት ለመጪው ትውልድ ለማስተላለፍ እንዲቻል ለባህሉ ቅርብ በመሆኑ የጥናቶችን ርዕስ ማጥናት ባህሎችን ጠብቆ ለማቆየት ጉልህ አስተዋጽኦ ይኖራቸዋል፡፡ ከነዚህም መካከል ሀገረ ሰባዊ ትውን ጥበብ እና ሀገረ ሰባዊ ድራማ ትልቁን ስፍራ ይይዛሉ፡፡ ሀገረ ሰባዊ ድራማ ባህልን ጠብቆ የመቆየት ሀገር ከፍተኛ ድርሻ ይወስዳል፡፡ ስለዚህ የጋሞ የግጭት አፈታት በአለም ድራማ ክንዋኔዎች አሉት፡፡

ቱጌ (ጋሻ) ግጭትን ለማብረድ ሽማግሌዎች ሚጠቀሙበት መከላከያ መሳሪያ ነው፡፡ ሽማግሌዎች በግጭቱ መሀል ገብተው እንዳይጋጩ፣ እንዳይገዳደሉ፣ ንብረት እንዳያወድሙ፣ በባህላቸው መሰረት እንደሚዳኝዋቸው እና ችግራቸውን እንደሚፈቱላቸው በመግለጽ በአካባቢያቸውን ያገኙትን እርጥብ ሳርን ሆነ ልብስ፣ ጋቢም ሆነ ቡሉኮ፣ ኩታም ሆነ የእንስሳት ቆዳ በመያዝ እንጨት ላይ ቱጌ ያቆማሉ ግጭቱንም በማስቆም ይዳኛሉ፡፡

ለምሳሌ፡- በጋሞ ብሄረሰብ የግጭት አፈታት ላይ ጉታ ጭማ ቴታ የሚባለው የግጭት አፈታት ስነ ስርዓት ሁለት ግለሰብ ሲጣሉ የሚያስታርቁት ቀለል ያለ የግጭት አፈታት ነው፡፡ እንዲሁም ደግሞ የግድያ ያልሆነ ወጣቶች በንግግር እና በንዴት የሚጣሉበት በጉታ ጭማ ቴታ ስነ ስርዓት ይፈታል፡፡ ይህ የግጭት አፈታት ጉታ ጭማ ቴታ ይባላል፡፡ ሌላው ደግሞ በድንበር የሚጣሉ ከሆነ እና ግጭታቸው ከፍ ሲል ወደ ዱቡሻ የግጭት አፈታት ይሄዳል፡፡ ይህ የግጭት አፈታት ከጉታ ጭማ ቴታ ከፍ ሲል የሚደረግ የግጭት አፈታት ነው፡፡

### 1.1. የጥናቱ ዳራ

በሀገራችን ኢትዮጵያ ብዙ አይነት ባህል፣ ወግ፣ ልማድ አሉ፡፡ በየብሄራቸው የራሳቸው የሆነ የአኗኗር ዘይቤ፣ አለባበስ፣ አመጋገብ እምነት ለማዶች አሉ፡፡  እነዚህን ጠብቆ ለማቆየት ሀገረ ሰባዊ ትውን ጥበቦች ይገኛሉ፡፡ ምሁራኖች እንደሚገልጹት ሀገረ ሰባዊ ድራማ በዚህ ዘርፍ ባህሎችን ብናጠና ለመድረክ ብናበቃ ባህሎች ከስር መሰረቱ ተጠንተው ስለሚጠኑ ባህሎቻችን እንዳይበረዙ ይረዳናል፡፡ ምክንያቱም በሀገረ ሰባዊ ትውን ጥበብ እና በ ሀገረ ሰባዊ ድራማ ዘርፍ ሲጠና በጥልቀት ባህሉን ከመሰረቱ ጀምሮ ተጠንቶ ብያኔ የሚሰጥበት እና የሚቀመጥ ነው፡፡ ከዚህ ዘርፍ ውጪ ሌሎች ለባህሎች ቅርብ የሆኑ ዘርፎች አሉ ለምሳሌ፡- የመድረክ ቴያትር ትራድሽናል (ትውፊታዊ) ቴአትር እነዚህ ለባህሎች ቅርብ ናቸው፡፡

አጥኝዋ ይህንን ጥናት እንድታጠና ያነሳሳት ምክንያት የጋሞ ግጭት አፈታት ከሀገራችን ኢትዮጵያ አልፎም በአለም ደረጃ እንዲታወቅ እና ባህሉን ቢያውቁት እጅግ በጣም እንደሚጠቀሙበት እና ይህ ባህል የመድረክ ቴያትር

ትራድሽናል (ትውፊታዊ) ቴአትር እነዚህ ለባህሎች ቅርብ ስለሆኑ ለአለም በድራማ መልክ ቀርበው ባህሉን ቢያውቁት በሰነድ ቢቀመጥ ለማሳወቅ ይረዳናል፡፡ (የአዲስ አበባ ከተማ የጋሞ ልማት ማህበር ማስተባበሪያ የ2012 ዓ.ም የባህል ቋንቋ ስምፓዚየም ንቅናቄ የተዘጋጀ)

### 1.2. የጥናቱ ዓላማ

#### 1.2.1. ዋና ዓላማ

የዚህ ጥናታዊ ጹሁፍ ዋና ዓላማው የጋሞ የግጭት አፈታት ከሀገረሰባዊ ድራማ አላባውያን አንጻር መተንተን ነው፡፡

#### 1.2.2. ንዑስ ዓላማ

- የጋሞ የግጭት ስነ ስርዓት ምን እንደሚመስል ማስቃኘት
- የጋሞ ሽማግሌዎች ግጭቱ ላይ ያላቸውን ሚና ማሳየት
- ዋና ባህሉን በማጥናት ዶክመንት ማድረግ እና ማሳወቅ፡፡
- ባህሉ እንዳይበረዝ፣ እንዳይረሳ ማድረግ
- ስለ ጋሞ ግጭት አፈታት ስነ ስርዓት ከሀገረሰባዊ ድራማ አላባውያን አንጻር ምን እንደሚመስል መተንተን
- ስለ ጋሞ ግጭት አፈታት ከግለሰቦች በቃለመጠየቅ መረጃ መሰብሰብ
- የጥናቱን ውጤት እና መፍትሄ ሀሳቦችን ማስቀመጥ

### 1.3. የጥናቱ ጠቀሜታ

#### 1.3.1. ዋና ጠቀሜታ

የጋሞ ግጭት አፈታትን ከስር መሰረቱ አጥንታ በመውሰድ (በሰነድ) ማሳወቅ እና ዶክመንት እንዲኖር ማድረግ፡፡

#### 1.3.2. ንዑስ ጠቀሜታ

የጋሞ የእርቅ ስነ ስርዓት ምን እንደሚመስል ማስቃኘት ዋና ባህሉን በማጥናት ዶክመንት ማድረግ እና ማሳወቅ፡፡ ባህሉ እንዳይበረዝ፣ እንዳይረሳ ማድረግ ነው፡፡ ሌሎች አጥኚዎች መነሻ ሀሳብ እንዲሆናቸው በሰነድ ማስቀመጥ ሀገር በቀል ድራማ ጥበብ ለሀገር ባህሎቻችን ያለውን ቅርበትና ጠቀሜታ ማስቃኘት፡፡

### 1.4. የጥናቱ ወሰን

ይህ ጥናታዊ ፅሁፍ በጋሞ ጎፋ ዞን አርባ ምንጭ ከተማ 40 ኪ.ሜ የሚገኘው ዶርዜ ላይ የሚደረገውን የጋሞ ሀገረሰባዊ ግጭት አፈታት ከሀገረሰባዊ ድራማ አላባውያን አንጻር መተንተን ነው፡፡ ምክንያቱም ይህ ሀገረሰባዊ ግጭት አፈታት የሀገረሰባዊ ድራማ አላባውያን አሉት ብላ አጥኝዋ ስለምታምን ነው፡፡

### 1.5. የጥናቱ ዘዴ

#### 1.5.1. የመረጃ አሰባሰብ ዘዴ

- የጋሞ ግጭት አፈታት ሲከወን በቦታው ተገኝቼ ስነ ስርዓት ክንዋኔዎችን በመመልከት
- የጋሞ አባቶችን እና የጋሞ ተወላጅ ስለ ባህሉ ጠንቅቀው የሚያውቁት እና ከዚህ በፊት እርቅ ያደረጉትን ወጣቶች ቃለ መጠይቅ በማድረግ
- ገላጭ የምርምር ዘዴ መረጃን ለመስብሰብ ታትመው የተቀመጡ መጻህፍትን በመስበሰብ ምልከታ በውስጡ አካቶ የያዘ በመሆኑ አጥኝዋ ይህን ጥናታዊ ጽሁፍ ለመስራት ከግለሰቦች ማግኘት ያልቻለችውን መረጃ በግጭት አፈታት ዙሪያ ከተጻፉ መጻህፍቶች በመመልከት(የመስክ ምልከታ ጥናታዊ ጽሁፍ) የምጸራ ይሆናል፡፡

#### 1.5.2. የመረጃ መተንተኛ ዘዴ እና የጥናቱ አይነት

ይህ ጥናታዊ ጹሁፍ ገላጭ ከምንለው የጥናታዊ ጹሁፍ አይነት ይመደባል፡፡ አለም እሸቱ "መሰረታዊ የምርምርና የዘገባ ዘዴ" በተሰኘ መጽሃፍ ገላጭ ምርምርን እንዲህ ሲል ያብራራዋል፡፡ ገላጭ የምርምር አይነት አንድን ችግር በምርምር መልክ አጣርቶ ለችግሩም ማረጋገጭ እና መፍትሄ የሚሰጥ የምርምር አይነት ነው፡፡ ገላጭ የምርምር አይነት አንድን ምርምር አጥንቶ መፍትሄ ለመሰጠት ብዙ ጥያቄዎችን አንስቶ ምን? ምንድነው? እያለ ለማብራራት ይሞክራል፡፡ ገላጭ ምርመር ትንታኔን፣ ገለጻን እና አተረጓጎም መሰረት የሚያደርገ ሲሆን በሁለት ተለዋዋጭ መሀከል ያለዉን ተዛምዶ እያወዳደረና እያነጻጸረ ሊመለከት ይችላል፡፡ ይህ የጋሞ የግጭት አፈታት ስነ ስርዓት የሚጠናበት ዘዴም ገላጭ የምርምር ዘዴ ይሆናል፡፡ ምክንያቱም ገላጭ የምርምር ሁለት ተዛምዶ ያላቸውን ሀሳቦችን በማንሳት በመሀከላቸው ያለውን አንድነት እና ልዩነት የሚያጤን በመሆኑ ነው፡፡

### 1.6. የጥናቱ አወቃቅር

ይህ ጥናታዊ ፅሁፍ በአራት ምዕራፎች የተከፈለ ነው ፡፡ ምዕራፍ አንድ መግቢያ፣ የጥናቱ ዳራ፣ የጥናቱ ዓላማ፣ የጥናቱ ጠቀሜታ፣ የጥናቱ ወሰን፣ የጥናቱ ዘዴ፣ የጥናቱ አወቃቀር፣ የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት፣ ጥናቱ የሚያነሳቸው ጥያቄዎች፣ በጥናት ወቅት ያጋጠሙ ችግሮችና መፍትሄዎች ሲሆን በምዕራፍ ሁለት የሃገረሰባዊ ትውን ጥበብ ምንነት፣ ሀገረሰባዊ ሙዚቃ ምንነት ፣ ሀገረሰባዊ ዳንስ ፣ ሀገረሰባዊ ድራማ ምንነትን ያካተተ ሲሆን በምዕራፍ ሶስት የጋሞ መልካዓ ምድር አቀማመጥ፣ የጋሞ የግጭት አፈታት ስነ ስርዓት፣ የቱጌ ግጭት አፈታት ዘዴ፣ የዱቡሻ ጭማ ቴታ ግጭት አፈታት፣ የግጭት መንስኤዎች፣ ኢኮኖሚያዊ እና የማህበራዊ የግጭት መንስኤዎች፣ግጭቶችን የማርገብ ስራ የሚሰሩ ባህላዊ መሪዎች፣ ግጭትና ባህላዊ የግጭት መፍቻ ዘዴዎች ሲሆን በምዕራፍ አራት አጠቃሎ( አጠቃሎ በቀዳማይ ክፍል የሚካተት ነው) ፣ ማጠቃለያ፣ የመፍትሄ ሀሳብ እና ዋቢ መፅሐፍትን ዝርዝር የሚያካትት ነው ፡፡

## 1.7. የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት

በሀገራችን የሚገኙ ባህሎቻችን በአሁኑ ሰዓት እየተረሱ እየተበረዙ እየጠፉ ይገኛሉ፡፡ እነዚህን ለመከላከል እና ጠብቆ ለማቆየት ሲባል የጋሞ የግጭት አፈታት ስነ-ስርዓት ለሀገረሰባዊ ድራማ ዘርፍ የቀረበ በመሆኑ ፤ በጋሞ ጎፋ ባህልና ቱሪዝም የሚዳሰሱና የማይዳሰሱ ቅርሶች በሚል ርዕስ የሚጠኑ ጥናቶች እትም ውስጥ ስለእርቅ በጥልቀት አለመዳሰሱ ፤ አጥኚዋ ሀገረሰባዊ ድራማ ለባህል የበለጠ ቅርብ መሆኑን ስለተገነዘበች ለማጥናት ተነስታለች፡፡

## 1.8. ጥናቱ የሚያነሳቸው ጥያቄዎች

- ሀገር በቀል ጥበብ ምንድነው?
- ሀገር በቀል ድራማ ምንነት?
- ሀገር በቀል ድራማ ምንድነው?
- ሀገር በቀል ሙዚቃ ምንድነው?
- የጋሞ የግጭት አፈታትምን ይመስላል?
- የጋሞ ሀገር በቀል የግጭት አፈታት ከቱውፍታዊ ተውኔት አላባውያን አንፃር ምን ይመስላል?

## 1.9. በጥናቱ ወቅት ያጋጠሙ ችግሮች

- በቂ መረጃ ያለመኖር
- በሀገራችን ስለ ሀገረሰብ ድራማ የተጻፉ መጽሀፎች አለመኖር
- በዩኒቨርሲቲዉ ለጥናታዊ ፅሁፍ የሚሆን መጽሀፍት እጥረት

### 1.9.1. የተወሰዱ መፍትሄ

- ✓ አጥኝዋ በተቻላት አቅም መረጃዎች ለማግኘት ሞክራ ባገኘቻቸዉ መረጃዎች ለመስራት ችላለች፡፡
- ✓ መፅሀፍትን ለማግኘት በአርባ ምንጭ ለአስራ ስምንት ቀን በማፈላለግ ባገኘቻቸዉ መፅሀፍቶች ለመስራት ችላለች፡፡
- ✓ በተለያዩ መፅሀፎች ዉስጥ ስለ ሀገረሰባዊ ድራማ የተፃፉትን በማንበብ አፈላልጋ ለመስራት ችላለች፡፡
- ✓ ባለሙያዎችን ለማግኘት ሌሎች ስራዎችን በመተዉ በመጠበቅ በስልክ በማግኘት መስራት ችላለች፡፡

## ምዕራፍ ሁለት

## የተዛማጅ ጹሁፎች ቅኝት

### 2.1. የተዛማጅ ጹሁፎች ቅኝት

የዚህ ጥናታዊ ጹሁፎች የተዛማጅ ጹሁፎች ክፍል ትኩረቱን የሚያደርገው ከጥናታዊ ጹሁፍ ጋር በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ የሚገናኙ የተለያዩ ሰዎች የጻፉዋቸው ስለ ሀገረሰባዊ ድራማ፣ ስለ ሀገረሰባዊ ትውን ጥበብ፣ ስለ ሀገረሰባዊ ዳንስ (ውዝዋዜ) የሚያትቱ የጋሞን ማህበረሰብ የግጭት አፈታት ለመተንተን ከሀገረሰባዊ ድራማ አንጻር ለመገምገም አስፈላጊ መሆናቸው አጥኚዋ አምናለች፡፡

### 2.2.የሀገር በቀል ድራማ ምንነት

ሀገረሰባዊ ድራማ ማለት እንደ ሌሎቹ የሀገረሰብ ጥበብ፣ የሀገረሰቡን ማንነት፣ ምንነት፣ እምነት፣ ባህል በሚገልጽ መልኩ የጋሞ የሆኑ ማህበረሰብ ብቻ የጋራ የሆኑ ክንዋኔዎች ከሌሎች ሀገረሰባዊ ክንዋኔዎች ተቀነባብረው ማህበረሰቡን የሚያንጸባርቅ፣ የሚያሳውቅ፣ የሚያስተዋውቅ እንደሆነ ተረድታለች፡፡ እንዲሁም ደግሞ የሀገረሰባዊ ድራማ )ምንነትን በተመለከት የተለያዩ ባለሙያዎች የራሳቸውን ብያኔ ይሰጣሉ፡፡ ነገር ግን ''ፎክ" እና "ድራማ" የሚሉት ቃላት በራሳቸው አከራካሪ ጽንሰ ሀሳብን የሚገልጹ በመሆናቸው ስለ ሀገረሰባዊ ድራማ ምንነት በግልጽ ብያኔ ለመስጠት አዳጋች ነው፡፡ ስለሆነም ጽንሰ ሀሳብን በተወሰነ ደረጃ ለመርዳት እንዲያመቹን የተወሰኑ የሀገረሰባዊ ድራማ ባህሪያትን ቀጥለን እንመልከት፡፡ ሀገረሰባዊ ድራማ በአንድ በተወሰነ ማህረሰብ ወይም ፎክ ቡድን ውስጥ የሚገኝ እና አንድ ማህበራዊ ጉዳይን መነሻ በማድረግ የሚቀርብ ክወና ነው፡፡ የሀገረሰባዊ ድራማ ከዋኞች የማህረሰቡ አባላት በመሆናቸው አብዛኞቹ ተመልካቾች የሚያውቋቸው እንዲሆኑ በድራማው የሚቀርብ ታሪክም ምልልስን እና እንቅስቃሴን መሰረት በማድረግ እንዲሆን ይህንንም አብርሃምስ (1972) ይገልጻል፡፡ (ፎክለር ሰለሞን ተሾመ ባዬ 2007 ዓ.ም)

### ሀገር በቀል ትውን ጥበብ

ሀገረሰባዊ ትውን ጥበብ የተለያዩ መጽሀፎች ሙሁራን በመጻፉቸው ገልጸዋል፡፡ ከእነዚህም አጥኚዋ እንደሚከተለው ታስቀምጣለች (ፍቃዱ አዘዘ የስነ ቃል መምሪያ ጥር 1991) በሚለው መጽሀፍ አስቀምጧል፡፡

ሀገረሰባዊ ትውን ጥበብበዚህ የጥልቅ ስም የምንጠራዊ ሀገረሰባዊ ሙዚቃ፣ ሀገረሰባዊ ዳንስ፣ ሀገረሰባዊ ድራማ የሚያጠናውን ሙያ እና የሚያጠኑትን ነገሮች ነው፡፡ እንግዲህ ይህ ከላይ የተጠቀሰው ሀሳብ ሀገረሰባዊ ትውን ጥበብ በውስጡ ሀገረሰባዊ ሙዚቃ፣ ሀገረሰባዊ ዳንስ እና ሀገረሰባዊ ድራማ አካቶ በሀገረሰባዊ ልብስ እና ቁሳቁስ ታጅቦ አስፈላጊ ዝግጅቶችን ተደርገው የሚከናወን እና የሚከወነውን የሚያጠና ነው፡፡ ከዚህ ሀሳብ በመነሳት አጥኘዋ ሀገረሰባዊ ትውን ጥበብ፣ ሀገረሰባዊ አልባሳት፣ ቁሳቁስ ተለብሶ ተይዞ ሀገረሰባዊ ትውን ጥበብ ድራማን በማዋሀድ

ዝግጅት ተደርጎበት የሚከወን እንደሆነ ተረድታለች፡፡ ሌላው ደግሞ (ፍቃደ አዘዘ) በዚሁ ጽሁፍስለ ሶስቱ አንድነት እንዲ ብሏል፡፡

ሙዚቃ፣ ዳንስ እና ድራማ ከፍ ብለን እንደዘረዝርናቸው ብቻቸውን የቆሙ አይደሉም በተግባር ጊዜ አንዱ በአንዱ ውስጥ ይኖራል፡፡ አንዱ ያለሌላው የሚኖሩበት ጊዜ አለ የሀገረሰብ ዘፈን ያለ ዳንስ (እስክታ ወዘተ... የሚከወንበት ጊዜ ማሰብ ያስቸግራል፡፡ እስክታው እና ድራማው ስላለው ከዚያ ማዕዘንም ሊጠና ይችላል፡፡) (ደራሲ ገጽ)

ከዚህ ጽሁፍ አጥኚዋ እንደተረዳችው ሀገረሰባዊ ትውን ጥበብ ውስጥ የሚገኙ ሙዚቃ፣ ዳንስ እና ድራማ በአንድ ላይ ተዋቅረው በአንዱ ውስጥ አንዱን ማግኘት እንችላለን፡፡ የሀገረሰባዊ ሙዚቃ ከሀገረሰባዊ ዳንስ ጋር በመዋቀር ሲቀርብ ወይም ሀገረሰባዊ ዳንስ ሲከወን ድራማዊ ድርጊያዎች እንዳሉበት ለመረዳት ያስችለናል፡፡አጥኚዋ ከዚህ ጽሁፍ ይህንን ተረድታለች እንዲሁም ደግሞ ሀገረሰባዊ ድራማ በሀገረሰባዊ ትውን ጥበብ ውስጥ ይገኛል፡፡ ሀገረሰባዊ ትውን ጥበብ ደግሞ ሶስት ነገሮችን ይይዛል፡፡ እነርሱም

- ✓ ሀገር በቀላዊ ሙዚቃ
- ✓ ሀገር በቀላዊ ዳንስ
- ✓ ሀገር በቀላዊ ድራማ ናቸው፡፡

**ሀገር በቀላዊ ድራማ**

ድራማ አንድ ታሪክን መሰረት በማድረግ የተለያዩ ገጸ ባህሪያት የታሪክ ባለቤት በማድረግ በመድረክ ላይ በመከወን ለታዳሚ የሚቀርብ ጥበብ ነው፡፡ በተለያዩ የዘርፍ ባለሙያዎች የድራማ አይነቶች እና በተለያዩ መንገድ ይከፍላችዋል፡፡ ከነዚህ መካከል ሮጀር አብርሀምስ (1972 ፡ 354) የድራማ አይነቶችን ሀገረሰባዊ ድራማ ታዋቂ ድራማ እና ውስብስብ ድራማ በሚል በሶስት ይመድባቸዋል፡፡ ከእነዚህም ምደባዎች መካከል የሀገረሰባዊ ትውን ጥበብ ዘርፍ ስለሆነው ስለሀገረሰባዊ ድራማ ምንነት እና ባህሪ ቀጥለን እንመለከታለን፡፡

ሀገረሰባዊ ድራማ በአንድ በተወሰነ ማህበረሰብ ወይም ፎክ ቡድን ውስጥ የሚከወን አይደሉም፡፡ ድራማው ስርዓተ ከበራዎች ክብረ በዓሎች፣ ፌስቲቫሎች፣ ሙዚቃዎች፣ ውዝዋዜዎች፣ ስነ ቃሎች፣ ጫወታዎች፣ እምነቶች ሌሎች የፎክለር አይነቶች በሚከወኑበት ወቅት ባሉ ውዝዋዜዎች፣ ንግግሮች እና ትምህርቶች አማካኝነት ማህበረሰቡ በጋራ የሚከወኑ ነው፡፡

ሀገረሰባዊ ድራማ በሀገረሰባዊ ትውን ጥበብ ውስጥ ከሚገኙ የጥበብ አይነቶች አንዱ ሲሆን ሀገረሰባዊ ዳንስ ከሀገረሰባዊ ሙዚቃ ጋር ተዋህዶ እንደሚቀርብ ሁሉ ከላይ በተጠቀሱ ሀሳቦች ሀገረሰባዊ በተለያዩ ክብረ በዓሎች ፌስቲቫሎች በሚቀርብበት ጊዜ (የሚከወንበት) ከሀገረሰባዊ ሙዚቃ እና ዳንስ ውስጥ ድራማዊ ድርጊያዎች እናገኛለን፡፡ ከላይ የተገለጸው ጽሁፍ (ሰለሞን ተሾመ ባዬ የሰዋ ሰው ችግር ፎክለር በሚለው መጽሀፉ)

በሌላኛው ክፍል ስለ ሀገረሰባዊ ድራማ እንዲህ ይላል፡፡ ሀገረሰባዊ ድራማ ራሱን ችሎ በማህረሰቡ ውስጥ የሚከወን አይደለም፡፡ ድራማዊ ስርዓት፣ ክብረ በዓሎች፣ ጨዋታዎች፣ እምነቶች፣ የፎክለር አይነቶች የሚከውን ነው፡፡ ይህን ሀሳብ ስንመለከት ሀገረሰባዊ ድራማ ከሌሎች ሀገረሰባዊ ከውኖች ጋር በአንድ ላይ በመሆን የሚከወን ሀገረሰቡ በተለያዩ ወቅቶች በተለያዩ ክብረ በዓሎች ውስጥ ከሀገረሰባዊ ሙዚቃ ከሀገረሰባዊ ዳንስ ጋር በመሆን ሀገረሰቡ እምነቱን ማንነቱን የሚገልጽ ድርጊቶችን ሲያከናውን በውስጡ ድራማዊ ድርጊያዎች አሉ፡፡ ይህም የሀገረሰቡን ማንነት እምነት፣ ባህል ምንነት በሚገልጽ መልኩ ማህበረሰቦች የጋራ የሆኑ ክንዋኔዎች ከሌሎች ሀገረሰባዊ ክንዋኔዎች ተቀነባብረው ማህበረሰቡን የሚያንጸባርቅ የሚያሳውቅ እንደሚሆን ተረድቻለው፡፡

ሌላው ደግሞ እነዚህ ሁሉ ሀገረሰባዊ ጥበብ ሲከወን ሀገረሰባዊ ቁሳቁስ ተይዞ ሀገረሰባዊ ቦታ ላይ ተገኝተው የሀገረሰቡ አባላት ከዋኞቹ ተዘጋጅተው ሀገረሰባዊ ቃለ ምልልሶች እየተደረጉ በዚህ በግጥማዊ ሀገረሰባዊ ድርጊቶች እየተወነ የሚቀርብ የሚታይ እንደሆነ ከላይ በተጠቀሰው መረዳት አይከብድም፡፡ በማህበረሰብ ውስጥ በተለያዩ ምክንያቶች ሀገረሰባዊ ድራማ በሚቀርብበት ወቅት በአድማጭ እና በከዋኙ መካከል የጠነከረ ግንኙነት አለ፡፡ ግንኙነቱም በእርስ በእርስ ምልልስ እና በጋራ ተሳትፎ የተዋቀረ ሲሆን ተመልካቾቹም ዝም ብለው ድርጊቱን የሚመለከቱ ሳይሆን ንቁ ተሳትፎ የሚያደርጉ ናቸው፡፡ ከዋኞቹም በሀገረሰባዊ ድራማው በሚል ልዩ ስልጣን የሚሰጣቸው አይደለም፡፡

አጥኝዋ ከዚህ ጽሁፍ እንደተረዳችው አንድ ባህል ለማስተዋወቅ በድራማዊ መልክ ሰዎችን ማስተማር በቀላሉ እየተዝናኑ ሳይሰላቹ ስለ ባህሉ በደንብ እንዲያውቁ እና በድራማዊ ድርጊያ ማህበረሰቡ ለማስተማር እንደሆነ ተረድታለች፡፡

**ሀገር በቀላዊ ሙዚቃ**

ሙዚቃን በሁለት መንገድ መክፈል እንችላለን ዘመናዊ እና ባህላዊ ሙዚቃ ሀገረሰባዊ ሙዚቃ ደግሞ ባህላዊ ሙዚቃ እንደሆነ መረዳት አይከብድም፡፡ ከዚህ ጋር በተያያዘ ስለ ሀገረሰባዊ ሙዚቃ ዘሪሁን አስፋው (የስነ ጽሁፍ መሰረታውያን በሚለው መጽሀፉ)

ባህላዊ ዘፈኖች በተለያዩ አጋጣሚዎች ላይ የሚዘፈኑት የማህበረሰቡ ልዩ ልዩ መልኮችን ሊያሳዩ የሚችሉ አስደሳች ስሜት መግለጫዎች ናቸው፡፡ ይህን ሀሳብ ስንመለከት ሙዚቃን ሙዚቃ ሊያስብል የሚያስችለው ዜማ እንደሆነ መረዳት ቀላል ነው፡፡ ስለዚህ ዜማ ወይም ሙዚቃ የሰው ልጆች ከተፈጠሩበት ጊዜ ጀምሮ እንደተፈጠረ ያስረዳል፡፡ ሙዚቃ ሰዎች ከተፈጠሩበት ጊዜ አንስቶ እንደ የአከባቢያቸው ይዘቱ፣ ስልቱ፣ ምቱ፣ ጣዕም ያላቸው የራሳቸው የሆነ ሀገረሰባዊ ሙዚቃ እንዳለ ሀገረሰባዊ ሙዚቃ የሀገረሰቡን ማንነት ምንነት እራሳቸውን በሚገልጥ ምት ሰልት ያለው እና ራሱን ማህበረስቡ ምንነት የሚገልጽ ድምጽ ነው፡፡ ሀገረሰባዊ ሙዚቃ ውስጥ የምናገኘው ግጥም በአብዛኛው የማህበረሰቡ ባህል፣ አለባበስ፣ ታሪክ ወዘተ የሚገልጽ ሀገር በቀል ዜማ (የቅኝት) ስልቶችን የሚጠቀም የድምጽ ምቱ

ባህላዊ የሆነ የሙዚቃ መሳሪያዎች ከአከባቢው በተገኙ ግዕባቶች የተሰሩ እና የማህረሰቡን ባህል የሚያንጸባርቁ ናቸው፡ ፡ ከእነዚህ ባህሪያት በተጨማሪ ጀፍ ቲቶን (1992፡ 167)

የሀገረሳባዊ ሙዚቃ በአንድ አከባቢ የሚኖር በተጨማሪም የዘር ሀረግ ያለውን ማህበረሰቡ ባህል መሰረት በማድረግ በቃል በማስተማር እና በማስታወስ ከትውልድ ወደ ትውልድ በቃል በማሰማት በክወና በማመልከት እንዲሁም በፊት ተግባቦት የሚተላለፍ በእለተ እለት ማህበራዊ ጉዳዮች ላይ የሚከወን እንደሆነይገልጻል (ሰለሞን ተሾመ ባዬ 2007 ፎክለር) በሚለው መጽሀፉ በጻፈው ያረጋግጥልናል፡፡

ስለዚህ አጥኝዋ ሀገረሰባዊ ሙዚቃ ከአንድ ማህበረሰብ በወጡ ግጥም፣ዜማ፣ ስልት፣ ምት የሙዚቃ መሳሪያዎች ተቀናብሮ በተለያየ ማህበረሰብ ክብረ በዓሎች ላይ የሚቀርብ የሀገረሰቡን ባህል ማንነት፣ እምነት፣ ታሪክ ወዘተ የሚገልጽ የሚያንጸባርቅ እንደሆነ አጥኝዋ ተረድታለች፡፡

**ሀገር በቀላዊ ዳንስ**

ሀገር በቀል ውዝዋዜ በአንድ ማህበረሰብ በራሱ ሀገር  በቀል ሙዚቃዎች ታጅቦ የራሱ ባህላዊ አልባሳት ለብሶ የራሱን ባህል የሚያንጸባርቅ የተለያዩ ቁሳቁሶችን በመያዝ የሚከወን ነው፡፡ ይህ ውዝዋዜ በአንድ በተወሰነ ማህበረሰብ ባህላዊ እና አከባቢ ድንበር ውስጥ የታጠረ እና የማህበረሰቡን ማንነት የሚያሳይ ነው፡፡

ማህበረሰቡ ከመደበኛ የተሳትፎ መንገድ እና ከመደበኛ ትምህርቶች ስልጠና ስርዓት ውጪ ለአባላቱ በማለማመድ እና በማሰልጠን ከትውልድ ወደ ትውልድ የሚያስተላልፏቸው ሀገረሰባዊ ውዝዋዜዎች በዋናነት የሚከወኑት ማህበረሰባዊ እና ሀይማኖታዊ ስርዓቶችን ለመፈጸም በሚከወኑት የተለያዩ ስርዓቶችን ለመፈጸም በሚል አላማ ነው፡፡ እነዚህን ማህበራዊ ሀይማኖታዊ ስርዓቶችን ለመፈጸም በሚል አላማ ነው፡፡ እነዚህን ማህበራዊ እና ሀይማኖታዊ ስርዓቶችን ለመፈጸም በሚከወንበት ጊዜ የተለያዩ ስርዓተ ከበራዎች ስነ ስርዓቶች፣ ፌስቲቫሎች፣ ሙዚቃዎች መሓል ሁነቶች ላይ የሚቀርቡ የተለያዩ ድርጊቶች በሀገረሰባዊ ውዝዋዜ ይቀርባሉ፡፡ (ሰለሞን ተሾመ ባዬ 2007 ፎክለር በሚለው መጽሀፍ) እንዲህ ገልጾታል፡፡

ስለዚህ አጥኝዋ ሀገረሰባዊ ዳንስ በአንድ አከባቢ የሚኖር የጋራ የሆነ ነገር ያላቸው ማህበረሰብ የራሱ የሆነ ሀገረሰባዊ አልባስ፣ ቁሳቁስ በመያዝና በመልበስ ከሀገርሰባዊ ሙዚቃ ጋር በመዋቀር የማህበረሰቡን ምንነት፣ ባህል፣ ታርክ፣ የኑሮ ዘይቤ፣ አስተሳሰብ ሳይቀር የሚያንጸባርቅ፣ የሚያሳይ እንደሆነ ለመረዳት ችላለች፡፡

## ምራዕፍ ሶስት

## የመረጃዎች ትንታኔ

### 3.1. የጋሞ መልካዓ ምድራዊ አቀማመጥ

የጋሞ አከባቢ በደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ የሚገኙ ተራራዎች ምድብ ውስጥ የሚካተት ሲሆን በምድቡ ትልቅ ከፍታ ያለው ጉጌ ተራራን ያጠቃልላል፡፡ ይህ አከባቢ በአብዛኛው ተራራማ በሆኑ ብዙ ጸሀፊዎች በተልምዶ የጋሞ ተራራማ መሬት በማለት ይገለጻል፡፡ አከባቢው ከባህር ወለል ያለው ከፍታ 850 ሜትር (ከኦሞ ሸለቆ ውስጥ) እስከ 4200 ሜትር (በጉጌ) ተራራ ላይ ነው፡፡ ጉጌ የሚለው የአከባቢው ስያሜ የተሰጠውም በአከባቢው ካሉ ተራሮች ሁሉ ከፍ ብሎ ስለሚታይ ነው፡፡ <u>(የጋሞ ጎፋ ህዝቦች ታሪክ ከጥንት ጀምሮ እስከ 1974) 2004 አርባምንጭ</u>

እንዲሁም ደግሞ የጋሞ ጎፋ ዞን በደቡብ ብ/ብ/ህ ክልላዊ መንግስት በደቡብ ማዕከላዊ አከባቢ የሚገኝ ከክልሉ ቆዳ ስፋት 10% የሚሸፍን ነው፡፡ የአከባቢው ተፈጥሮአዊ መልካ ምድር ተራራማ መሬቶች የበዛበት እና አብዛኛው ደጋማ ወይናደጋ አየር ንብረት የሚያጠቃልል ነው፡፡ በዞኑ ኦሞአዊ ቋንቋ ተናጋሪዎች የሆኑ የጋሞ ጎፋ፣ ኦዳ እና ዘይሴ ብሄረሰቦች እና የኩሽ ቋንቋ ተናጋሪዎች የሆነው የጊዲቾ ብሄረሰብ በአንድነት ይኖራሉ፡፡ ታሪካዊ አሰፋፈራቸውም ኩታ ገጠም በሆነ መሬት ላይ እስከ 19ነኛው መቶ ክፍለ ዘመን መጨረሻ ድረስ የራሳቸው ባህላዊ አስተዳደር የነበራቸው ናቸው፡፡ ከዚህም በማዕከላዊ የኢትዮጵያ መንግስት ስርዓት በተዘረጋው የ1930ዎቹ መዋቅር መሰረት አውራጃዎች፣ ወረዳዎች እንዲሁም ጠቅላይ ግዛትና ክፍለ ሀገር የሚል የአስተዳድር መዋቅር ስም እያገኘ የመጣ አከባቢ ነው፡፡

ብሄረሰቦቹ በረጅም ዘመናት የአኗኗር የተቀራረበ፣ የጠበቀ ትስስር እና ባህላዊ እሴቶችን በማዳበር የኖሩ ናቸው መተዳደሪያቸው በዋናነት ጥምር ግብርና ሲሆን በተጨማሪ ለጋሞ ብሄረሰብ የሽመና ስራውም መተዳደሪያው ነው፡፡ በአሁኑ ሰዓት የጋሞ ጎፋ ዞን 15 የወረዳ እና 2 የከተማ አስተዳደር መዋቅሮች ያሉት ሲሆን ከነዚህም ውስጥ የጋሞ ብሄረሰብ በ9 ወረዳዎች ማለትም በአርባ ምንጭ ዙሪያ፣ በምዕራብ አባያ፣ በካምባ፣ በድራማሎ፣ በቁጫ፣ በቦረዳ፣ በዲታ፣ በቦንኬና በጭንቻ ወረዳዎችና በአርባምንጭ ከተማ በነባርነት ተዋቅሮ ይኖራል፡፡

በ1999 ኢ.ም የማዕከላዊ ስታትኪስ ባለስልጣን የህዝብና ቤት ቆጠራ መሰረት የጋሞ ብሄረሰብ የህዝብ ብዛት 1107163 ነው፡፡ የጋሞ ብሄረሰቦች የሚኖሩባቸው ወረዳዎች በአብዛኛው ደጋማና ወይናደጋ የአየር ንብረት ክልሎች ናቸው፡፡ በእነዚህ አከባቢዎች እንሰት፣ ገብስ፣ ስንዴ፣ ስራስር፣ ጥራጥሬ፣ ፍራፍሬ፣ ቅመማ ቅመም ይመረታል፡፡ የጋሞ አከባቢ ተፈጥሮ የመሬት አቀማመጥ ተራራማ የሆነ እና በአመት ሁለት የዝናብ ወቅቶች ሚፈራረቅበት ነው፡፡

በዚሁ ከምስራቅ የስምጥ ሸለቆ ሀይቆች አባያና ጫሞ ከደቡብ ወደ ወይጦ የሚፈሱ ትልልቅ ወንዞች በምዕራብ ደግሞ የኦሞ ወንዝ ገባሪ ጅረቶች መነሻ ቦታ ነው፡፡ ብሄረሰቡ የሽመና ስራ ቴክኖሎጂ አመንጪ በመሆን የዞኑና የሌሎች

አከባቢዎች ብሄረሰቦች የልብስ ፍላጎት ከማሟላት ባሻገር በአገር ረጃጅም በዚሁ ጥበብ ይታወቃል፡፡ (ቢጋሞ ጎፋ ዞን ማስታወቂያና ባህል መምሪያ ታህሳስ 2001 አርባ ምንጭ) ግጽ 28

የጋሞ ሰንሰለታማ ተራሮች አጠቃላይ አቀማመጥ ከሰሜን ወደ ደቡብ ምዕራብ የተዘረጋ ሆኖ በርካታ ከምስራቅ ወደ ምዕራብ የተዘረጉ እና ከፍታቸው በፍጥነት እየቀነሰ ዙሪያው ወዳሉ የስምጥ ሸለቆ፣ ማዜ፣ ማሌና አዳቡሻዬ ዝቅታማ ቦታዎች የሚወርዱ ከፍታ ቦታዎች ይገኙበታል፡፡ ተራሮች በየአከባቢው በትልቅነታቸው የሚታወቁ አዶሽካዬ ዝቅታማ ቦታዎች የሚወርዱ ከፍታ ቦታዎች ይገኙባቸዋል፡፡

ተራሮች በአከባቢው ትልቅነታቸው በሚታወቁ አዶሽካዬ፣ ሳጉ፣ ሲሌ፣ ኩልፎ፣ ሀሬ፣ ደሜ፣ ማስታ፣ ከቦረዳ እስከ ጋርዱላ ያለው አከባቢ ጋሞ ተብሎ ስለመጠራቱም እንዳቸሩል የተባለው ጸሀፍ እንደሚከተለው አስቀምጧል፡፡

ይህም የመሬቱ አቀማመጥ በተለይ ከፍታው ከባህር ወለል 2000 ሜትር በላይ እየጨመረ ሲሄድ ተራሮች የተጠራቀመ ውሀ እንደሚሰራው ማዕበል ከፍና ዝቅ እያለ ትልቅ ጉብታና ጥልቅ ሸለቆዎች ይፈጥራል፡፡ ወደ ላይ የወጡትን ጉብታዎች ከሩቅ ሲታይ ሰው የሌለባቸው ይመስላሉ፡፡ በርግጥም አብዛኞቹ ሰው የሌለባቸው ነገር ግን ወደ ታች ዝቅ ያለው መሬት ከገጠር ይልቅ ወደ ከተማነት በሚያዘነብል አሰፋፈር ተሞልቶ ይታያል፡፡ ሁለት ኪሎሜትር በማይሞላ ርቀት ባላቸው ሁለት ጉብታዎች ውስጥ የሚቆጠሩ መኖሪያ ቤቶች ይታያሉ፡፡ የዚህም አይነት አሰፋፈር በተለየ በቦንኬ፣ ካምባ፣ አርባ ምንጭ ዙሪያ፣ በዲታ፣ ደራማሎ፣ እና ጩንቻ ወረዳዎች ደጋማ አከባቢዎች በስፋት የሚታይ አሰፋፈር ነው፡፡ በደገማው አከባቢ ለቤት መስሪያነት የሚያገለግለው ተክል ቀርከሀ ሲሆን ሁሉም የቤቱ አካል በአንዳንድ ቦታዎች ክዳኑ ሲቀር ግድግዳው፣ ጣሪያው፣ ዋልታው፣ ማገሩ፣ ማሰሪያው፣ መዝጊያው፣ አልጋው ከቀርከሃ የተሰራ ነው፡፡

በዲታ እና ዳራማሎ ደጋማ ቦታዎች በጨንቻ ወረዳዎች የቤት ክዳኑ የቀረከሃ ልባስ ስለሆነ በነዚህ ቦታዎች የቀርከሃ ዛፍ የተሟላ የቤት ግንባታ ጥሬ እቃ ነው፡፡ ስለዚህ የቀርከሃ ዛፍ እያንዳንዱ ነዋሪ ከእንሰት ቀጥሎ ትልቁ ትኩረት የሚሰጠው ተክል ነው፡፡ በደጋማው አከባቢ አንድ አባወራ በግቢ ውስጥ የመኖሪያ የበጎች ማደሪያ፣ የምግብ ማዘጋጃ፣ የእንግዳ መቀበያ፣ የእህል ማከማቻ ቤቶች ስለሚኖሩት ግብው የአንድ ቤተሰብ ሳይሆን አንድ ትንሽ መንደር ይመስላል፡፡ የቤቶቹ ብዛት እንደ ሀብት መጠን እና እንደ ቤተሰብ ብዛት ይጨምራል፡፡ በአከባቢው ላሻ ተብሎ የሚታወቀው አጥር ቤቶች  ከጓሮ በኩል አትክልት የሚለው ሲሆን በባለሙያ የሚታነጽ ነው፡፡

ላሻ ከጓሮ በኩል አንድ ጊዜ የሚዞር ሆኖ ከፊት ለፊት እንደ ባለቤቱ የሀብት መጠን ሶስት አራት ጊዜ የሚደራረብ እና በእያንዳንዱ መግቢያ በር ያለው ነው፡፡ የላሻ አጥር ወግ በህዝብ ቁጥር መጨመርና በቀርከሃ ተክል መመናመን በአንዳንድ አከባቢዎች እየቀነሰ ቢመጣም ደጋማ በሆኑ ቦታዎች አሁንም ይዘወተራል፡፡

### 3.1.1. የጋሞ የግጭት አፈታት ስነ- ስርዓት

በሀገር በቀል ባህላዊ ክንዋኔዎች በሰዎች ዘንድ ሲፈጠሩ የቆዩ መፍትሄ ሰጪ ለችግሮች ቢቀመሩ ፋይዳቸው ላቅ ያለ ነው፡፡ ግጭት ያለ የነበረ እና ወደፊትም የሚኖር በሰው ልጆች የህይወት እንቅስቃሴ ውስጥ የሚያጋጥም ክስተትም ሂደትም ነው፡፡ ግጭቶችን እና አለመግባብቶችን በየአከባቢው፣ በየማህበረሰብ እና በየብሄረሰቡ የተለያዩ የግጭት አፈታት የእርቅ ስርዓቶች አገልግሎት ላይ ይውላሉ፡፡ ጓደኛ ከጓደኛ ሲጋጭ ቤተሰብ ከቤተሰብ ሲጣላ ባልና ሚስት አለመግባባት ሲገጥማቸው እንዲሁም ህዝብ ከህዝብ ሲጋጭ እርቅ ይኖራል፡፡ በዚህ ረገድ የጋሞ ብሄረሰብ የሚያጋጥሙትን ግጭቶች እና አለመግባባቶች የሚፈታተበት ሌላው ማህረሰብ ተምሳሌት ሊሆን የሚችል ሀገረሰብ የግጭት አፈታት ስርዓት አለው፡፡ ይህ ስርዓት መች እንደተጀመረ በውል የሚይሳይ ሰነዶች የተቀመጠ መረጃ ባይኖርም ማህረሰቡ ሲፈጠር አብሮ እንደተፈጠሩ የሚናገሩ አፈታሪክ መረጃዎች ግን አልጠፉም፡፡ በጋሞ ብሄረሰብ የግጭት አፈታት ስርዓት ውስጥ ለእያንዳንዱ የግጭት አይነት ማህረሰቡ ተስማምቶ ያስቀመጠው ስርዓት አለ፡፡ ከነዚህም ስርዓቶች ውስጥ "የቱጌ" ስርዓት አንዱ ነው፡፡

### 3.1.2. የቱጌ የግጭት አፈታት ዘዴ

ቱጌ ግጭትን ለማብረድ ሽማግሌዎች የሚጠቀሙበት መከላከያ መሳሪያ ነው፡፡ ሽማግሌዎች በግጭቱ መሀል ገብተው እንዳይጋጩ፣ እንዳይገዳደሉ፣ ንብረት እንዳያወድሙ በባህላቸው መሰረት እንደሚዳኙዋቸው እና ችግራቸውን እንደሚፈቱላቸው በመግለጽ በአከባቢያቸው ያገኙትን እርጥብ ሳርም ሆነ ልብስ ጋቢም ሆነ ቡሉኮ፣ ኩታም ሆነ የእንስት ቆዳ በመያዝ እንጨት ላይ ቲጌ ያቆማሉ፡፡

ግጭትንም በማስቆም ይዳኛሉ እናቶችም በቦታው የተገኙ ከሆነ መቀነታቸውን በመፍታት መሀል ገብተው ይተኛሉ፡፡ /ታና ኤኪቴ ታና ኤኪቴ ታኒ ማራሞ ማሳታይስ/ እያሉ ይለምናሉ ይህም ማለት እኔን ውሰዱ እኔ ማርያምን እመስላለው ማርያምን ረግጠው መሄድ አይቻልም አትጋጩ በማለት ይማጸናሉ፡፡ በዚህ ስርዓት መሰረት የሚፈጠሩ ግጭቶች ይፈታሉ፡፡ በጋሞ ብሄረሰብ ብዙ ጊዜ ያልተጠበቀ ግጭት ሲፈጠር የሚጠራው "ኡሎ አላ ኡሎ አላ" በሚል ጩሀት ነው፡፡ ይህ ደግሞ የጭወት አይነት ነው፡፡ ጩሀቱን የሰማው የአከባቢው ሰው ደግሞ ይሰበሰባል፡፡ ግጭቱ የሁለት ደሬዎች ሆኖ የከፋ ግጭት የሆነ እንደሆነ በሬ በአካል ቱጌ ሆኖ ይቆማል፡፡

በዚህ ጊዜ የነሱን ልመና ተላልፎ ወደ ሁከት እና ብጥብጥ ውስጥ የሚገባ አካል አይኖርም፡፡ ምናልባት ካለ በማህበረሰቡ እምነት እና ባህል መሰረት ሀጥያት (ጉሜ) ይሆንበታል ተብሎ ይታመናል፡፡ በማህበረሰቡ ጎሜ የመጥፎ ስራ ክፍያ ነው፡፡ ይህ ጎሜ ማህበረሰቡ ተስማምቶ የኖረበትን ወግ ባህል እንዲሁም የማህበረሰቡ ሀገር ሽማግሌዎችን ልመና እና ተግጻጽ አሻፈረኝ ብሎ የሚወርድ ቁጣ እና ቅጣት እንደሆነ ይነገራል፡፡ በዚህ የእርቅ ስነ ስርዓት ወቅት የሚይዙት ሳር ተምሳሌትነቱ ሰላም ነው፡፡ የመከላከያ መሳሪያ ነው አባቶች ሳሩን ይዘው ሲለምኑ "አትንኩ" ብቻ አይደለም የሚሉት፤ ተቆጥታችዋል፣ ተጎድታችዋል፣ ስሜት ውስጥ ያስገባቹ ነገር አለ፣ ግን ታገሱ፣ ተመለሱ እንደ ተቆረጠው ሳር ሳይሆን እንደሚያድገው፣ እንደሚለመልመው "ሳር" ሁኑ ብሎ ይማጸኑበታል፡፡ በቱጌ ስርዓት ወቅት

የነብር ወይም የአንበሳ ቆዳ እና ትልቅ በሬ በአካል ተይዞ የሚደረገው ቱጌ እንደ ደሬ ከሌልላው ደሬ ድንበር ምክንያት ሲጋጭ እና ግጭቱ ወደ ለየለት ጦርነት የመግባት አዝማሚያ የሚያሳይ እንደሆነ ነው፡፡

ቱጌውን የሚያቆሙት ባህላዊ አባቶች ኢጋዴ፣ ጋና፣ ካሬ ወዘተ ተብለው ይጠራሉ፡፡ በጋሞ ብሄረሰብ አርባ ሁለት ደሬዎች አሉ፡፡ እነዚህም ደሬዎች የራሳቸው ወሰን አላቸው፡፡ አንዱ ደሬ ያንዱን ደሬ ወሰን፣ ሀብት ና ንብረት ላለመንካት፣ ላለመጎዳዳት መሃላ አላቸው፡፡ የመሃላው አንድምታ አንጋጭም፣ አንጣላም አንዳችን የአንዳችንን ወሰን ሀብት፣ ንብረት፣ ልጅ፣ ሚስት ወዘተ አንነካካም የተጣላን እንደሆነ በዚች በመሃላ ስፍራችን ቁጭ ብለን እንዳኛለን የሚል ነው፡፡ አባቶች በዚህ ጊዜ ቱጌውን የሚያቆሙት በተጋጪዎች ድንበር ላይ ነው፡፡ ግጭቱ ክስተት ሲሆን ማንኛውም አካል ገብቶ ቱጌ ማቆም እንደሚችል ያስረዳሉ፡፡ ሳይታሰብ በተፈጠረው ግጭት ግድያ ያለበት ከሆነ የገዳይ እና የሟች ወገን "ጎምፓ" (ከእርቅ በኋላ የሚፈጸም አብሮ መብላትና መጠጣት) በማድረግ እርቁ ይፈጸማል፡፡ በብሄረሰብ ውስጥ እስከ 300 የሚደርሱ ጎሳዎች እንዳሉ ይነገራል፡፡ ከነዚህ ጎሳዎች መካከል እርቁን የሚያከናውኑ ሽማግሌዎች ተመርጠው ይላካሉ፡፡ ሶስተኛ እና አራተኛ ዙር ሟች ቤተሰብ (ጎሳ) ጋር ተመላልሰው እሺ ካሰኙ በኋላ እርቁ እንዲፈጸም ያደርጋሉ፡፡ ለእርቁ ማሳረጊያ የእርድ ስነ ስርዓት ይደረጋል፡፡ እርዱን የሚፈጽመው ደግሞ ባህላዊ ቄስ "ማካ" ነው፡፡ ከታረደ በኋላ "ኮይራ ፍሬ" (የጎሳ መሪው) ከሟች እና ከገዳይ ጎሳ መሪ ጋር ደምና ፈርሱን በመርገጥ ሶስት ጊዜ ዮ......ዮ......ዮ...... (ዮ ማለት ሰላም አውርደናል እርቅ አድርገናል) በማለት ጎምፓ በማድረግ የተዘጋጀውን መብልና መጠጥ አብረው ይቋደሱታል፡፡ ከዚያም የግጭቱ አፈታት ተፈጸመ ማለት ነው፡፡ (ሻ ሆይ ባ በሚለው መጽሄት የካቲት 30/2012 ዓ.ም የባህል ቋንቋ እና ሲምፓዚየም ንቅናቄ የተዘጋጀ )

### 3.1.3. ዱቡሻ ጭማ ቴታ

ዱቡሻ ማለት የጋሞኛ ቃል ሲሆን ትርጉሙ ባህላዊ የህዝብ መሰባሰቢያ አደባባይ ማለት ነው፡፡ መሰባሰቢያው ቦታው ብዙሁኑ ህዝቦች ዘንድ የአንድነት እና የጥንካሬ መገለጫ ሲሆን የሚያገኘውን በየአንዳንዱ ባህላዊ መንደር ውስጥ ማዕከላዊ ስፍራ ላይ ከሌሎች አግልግሎቶች ነጻ በሆነ ስፍራ ላይ ነው፡፡ በባህላዊ፣ ፖለቲካ አስተዳደር ስርዓት መሰረት ህዝቡ ከመሪው ጋር ተገናኝቶ ህግ የሚያወጣበት መተዳደሪያ ደንብ የሚጸድቅበት የተጣሉ የሚታሩቁበት የእርቅ ስነ - ስርዓት የሚካሄድበት ባህላዊ ዳኝነት ባህላዊ ሹመት የሚካሄድበት መረጃ የሚለዋወጡበት ደመራ የሚያወጡበት ልጆች ስለ ባህላቸው እና ታሪካቸው የሚቀስሙበት በድብቅ የተፈጸሙ ወንጀሎች የሚጣሩበት የተከበረ ቦታ ነው፡፡ ሌላው ደግሞ በዱቡሻ ሚፈታው ነገር ጥሉ ከፍ ሲል እንደ ግድያ ደም መፋሰስ ከሆነ ከላይ እንደተገለጸው በዱበሻ ባህል ተሰብስበው እርቅ ይፈጽማሉ፡፡ ትልቁ የእርቅ ስነ-ስርዓት ስፍራ ነው፡፡

### 3.1.4. የግጭት መንስኤዎች

የጋሞ ብሄረሰብ በዞን ውስጥ አብረው ከሚኖሩ ከጎፋ፣ አይዳ፣ ዘይሴ፣ ከጊዲቾ እና ከሌሎች አጎራባች ብሄረሰቦች ጋር ለረጅም ዘመናት አብረው የኖሩ በመሆናቸው በማህበራዊ፣ በፖለቲካዊ፣ በኢኮኖሚያዊ እና በባህላዊ ዘርፎች ትስስር አላቸው፡፡ በብሄረሰቡ አከባቢ የሚፈጠሩ ግጭቶችና አለመግባባቶች መንስኤዎቻቸው ሌሎች አከባቢዎች ከሚከሰቱ

ግጭቶች ጋር በአንድም ሆነ በሌላ መንገድ ተመሳሳይነት ያላቸው ቢሆንም መንስኤዎቻቸው ኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊ፣ ባህላዊና እይታዊ ይዘት ያላቸው መሆኑን ይህ ጥናት ያመለክታል፡፡

### 3.1.5. ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ የግጭት መንስኤዎች

ለግጭቶች መንስኤ ከሚሆኑ ጉዳዮች መካከል አንዱ ወሰን የሆነውን የተፈጥሮ ሀብት ለመቆጣጠር በሚያደርገው ሽሚያ ነው፡፡ በጋሞ ብሄረሰብ ዘንድም የተፈጥሮ ሀብት ለመቆጣጠር ሲባል አለመግባባቶችና ግጭቶች እንደሚከሰቱ በጥናቱ የተሳተፉ መረጃ ሰጪዎች ይገልጻሉ፡፡ ለአብነትም መሬት ቋሚ የሆነ ውስን የሆነ የተፈጥሮ ሀብት ከመሆኑ ጋር ተያይዞ ይህን ውስን ሀብት ለመቀራመት ሲባል በአከባቢው አልፎ አልፎ ግጭቶች ይከሰታሉ፡፡ ከመሬት ጋር ከሚከሰቱ ግጭቶች መካከል የድንበር እና የግጦሽ ግጭቶች ዋነኖች ናቸው፡፡ በመሆኑም በጋሞ ብሄረሰብ ዘንድ "በሚስትና በርስት" ቀልድ የለም ተብሎ የሚነገር አባባል አለ ትርጓሜውም ርስቱ የተደፈረበት እና ሚስቱ የተደፈረችበት ሰው አንድ ነው ማለት እንደሆነ መረጃ ሰጪዎች ያስረዳሉ፡፡ ይህም የሚያመለክተው በብሄረሰቡ አከባቢ ያለው መሬት ፍትሃዊ በሆነ መንገድ ማስተዳደር ካልቻለ ለግጭቶች መንስኤ እንደሚሆን ነው፡፡

ሌላው ከመሬት ጋር ተያይዞ ጎሳን ከጎሳ ጋ የሚያጋጨው መሬትን መሸጥ ሲሆን በብሄረሰቡ ባህል የእኔ ነው ብሎ መሬት መሸጥ ወይም ለረጅም ጊዜ ማከራየት ክልክል ነው፡፡ አንድ ሰው መሬቱን ማከራየት ሲፈልግ ዘመዶቹን ማማከር የግድ ይጠበቅበታል፡፡ ይህ ብሄረሰቡ ለዘመናት የቆየውን መሬት እንዳይሸጥ የሚከለከለው ባህላዊ እሴት ከመንግስት ፖሊሲ ጋር ተጣጥሞ የሚሄድ እሴት ነው፡፡ በአከባቢው በኢኮኖሚ ችግርም ሆነ በሌላ ምክንያት የሚፈጸሙ ስርቆቶች ለግጭት መንስኤ ሊሆኑ እንደሚችሉ የጥናቱ መረጃ ሰጪዎች ያስረዳሉ፡፡ በጋሞ ብሄረሰብ አከባቢ የሚኖሩ ህዝቦች በተለያዩ አውዶች ማህበራዊ ግንኙነት ፈጥረው በጋራ የሚኖሩበት ሁኔታ ይስተዋላል፡፡ ለአብነትም የጋራ ገበያ መገበያየት፤ በጋብቻ መተሳሰር በለቅሶ፣ በሰርግ ወዘተ ግንኙነትን ይፈጥራል፡፡ ሆኖም ግን አልፎ አልፎ በነዚህ ማህበራዊ ግንኙነቶች ምክንያት አለመግባባቶች እና ግጭቶች እንደሚከሰቱ ያመለክታል፡፡

በጋሞ ብሄረሰብ በባህላዊ የለቅሶ ስነ-ስርዓት ላይ ብዙ ሰዎች በአንድ ጊዜ በፈረስ ወይም በበቅሎ ላይ ተቀምጠው ጦርና ጋሻ ይዘው ተንበርክከው የሚያለቅሱበት ባህላዊ ስርዓት ይላቸው ሲሆን በዚህ ወቅት ቀደም ብሎ የገባ ወገን አልቅሶ ሳይጨርስ ሌላ ወገን የሚገባ ከሆነ በመካከላቸው ግጭት እንደሚፈጠርና የተፈጠረውን ግጭትን ቶሎ የማይበርድ የግጭት አይነት እንደሆነ መረጃ ሰጪዎች ያስረዳሉ፡፡ በአከባቢው ከሚከሰቱ ግጭቶች አንዱ ከጋብቻ ጋር ተያይዞ የሚከሰት ግጭት ሲሆን ለአብነት አንዱ ያጫትን ልጅ አገረድ ሌላ ወንድ ካገባ የልጅቷ እጮኛ እና ቤተሰቦቿ እኛን ንቆ ነው ልጅቷን ያገባው በሚል ግጭት የሚቀሰቀስ ሲሆን ግጭቱ ወዲያውኑ ካልተፈታ ደግሞ ወደ ጎሳ ግጭት ሊሸጋገር እንደሚችል መረጃዎች ያስረዳሉ፡፡

### 3.1.6. ግጭቶችን የማርገብ ስራ የሚሰሩ ባህላዊ መሪዎች

አጋዴ፣ አጋሳጋና እና ካራ የተባሉ ባህላዊ መሪዎች በጋሞ ብሄረሰብ ዘንድ በተለያየ አከባቢዎች የተለያየ ስያሜ የተሰጣቸው ቢሆንም ዋና ተግባራቸው ግጭትችን ማርገብ ነው፡፡ አጋዴ የሚለው የቃሉ ትርጉም አጌ ወይም መንገድ ከሚለው የጋሞኛ ቃል የተወሰደ እንደሆነ መረጃ ሰጪዎች ይገልጻሉ፡፡ በተጨማሪም አጋዴ የሚለው ቃል በብሄረሰቡ አባላት ዘንድ የእርቅ መንገደኛ ወይም አገናኝ የሚለውን ትርጉም ይይዛል፡፡ በጋሞ ብሄረስብ ዘንድ አጋዴ ወይም አጋሳ ግጭቶችን የማርገብ እና የመፍታት የቆየ ባህላዊ እሴት እንዳላቸው እና እስካሁን ድረስ ህዝቡን እያገለገሉ ያሉ መሆኑን የጥናቱ መረጃ ሰጪዎች ይገልጻሉ፡፡

በጋሞ ብሄረሰብ ዘንድ አጋዴዎች የካዎ ግዛት በሚያዋስንባቸው ድንበሮች ሁሉ የሚሰየሙ ሲሆን በደሬዎች መካከል የሚከሰቱ አለመግባባቶች በአጋዴ /በጋና/ አማካኝነት እንደሚፈቱ ከእድሜ ባለጸጋዎች የተገኙ መረጃዎች ያስረዳሉ፡፡ አጋዴ የሚሰየመው በካዎ ሲሆን ተግባሩ የካዎ ግዛት ከውጪ ጋር ለሚያደርጋቸው ግንኙነቶች ከቤተሰብ ወይም ከጎሳ ብቁ የሆነ ሰው ተመርጦ በዘር በሚተላለፍ ሹመት ነው፡፡ (የጋሞ ጎፋ ዞን ማስታወቂያ ባህል መምሪያ 2004 ይገለጻል)

አጋዲዎች ግጭቶች እና ውጥረቶች በነገሱበት ሁኔታ መካከል ገብተው ግጭቶች እንዳይባባሱ በማድረግ ግጭቶችን የማስቆም ስራዎች እንደሚሰሩ ይታወቃል፡፡ ግጭቶችን ለማርገብ የሚጠቀሙበት በብሄረሰቡ ዘንድ ተቀባይነት ያላቸውን ምልክቶች በማሳየት ሲሆን እነዚህን ምልክቶች ከአንዱ አከባቢ ወደ ሌላው አከባቢ ይለያያሉ፡፡

በአንዳንድ የጋሞ አከባቢዎች በግጭት ወይም በጦርነት መሀል አጋዴዎች የበግ ለምድ ለብሰው ቆዳ እና ቱጌ የሚባል ብረት ይዘው ሲቆሙ በሌሎች አከባቢዎች በቀርከሃ እንጨት አናቱ ላይ ጨርቅ በማሰር ይዘው መካከል ላይ በመቆም ግጭቶችንን እና ጦርነቶችን የማስቆም ስራዎችን ይሰራሉ፡፡ በባህሉ መሰረት በግጭቶችና ጦርነቶች መሀል እነዚህን ምልክቶችን ይዞ መቆም ጥፋተኞች ነን የሚል መልዕክት እንዳለው መረጃ ሰጪዎች ይገልጻሉ፡፡

በጋሞ ብሄረሰብ ባህል አጋዴዎች ቱጌ፣ ጸንባሮ ወይም ሌላ በብሄረሰቡ ዘንድ ተቀባይነት ያለውን ምልክት ይዘው ከቆሙ በማንኛውም ጦርነት መሀል ሆነው እንኳ ከተጋጩ ወገኖች እነሱ ላይ ጥቃት አያደርሱባቸውም፡፡ ለዚህም ዋናው ምክንያት በግጭቶች ወይም በጦርነት ወቅት አጋዴ መሀል ላይ ቆመው እነሱን አልፎ ሄዶ ጦርነትን የሚቀጥል ወገን ቢኖር ያ ወገን በጦርነቱ ይሸነፋሉ ተብሎ ስለሚታመን ነው፡፡ አጋዴዎች ወይም አጋትሳ ሁለት የተጋጩ ወገኖችን በሚያደራድሩበት ወቅት የሁለቱንም ወገን አለቆች በድርድሩ እንዲሳተፍ በማድረግ ነው፡፡ ደም ያፈሰሰ ግጭት ከሆነ እርቅ ሰላም ለማወረድ ከሁለቱም ወገን በተዋጣው ገንዘብ ጦበት ተግዝቶ ወጋዴ በሚባሉ የማንጻት ስራ በሚሰሩ ሰዎች አማካኝነት እርድ እንዲፈጸም በማድረግ ደግሞ በቂም በቀል እና በደም እንዳይፈላለጉና እንደቀድሙቸው በሰላም አብረው እንዲኖሩ የመሃላ ስርዓት በማስገባት በአጋዴዎች አማካኝነት እርቅ ሰላም ይፈጸማል፡፡

በአጋዴዎች የሚፈቱት አለመግባባቶች ግጭቶች የሚወሰነው በግጭቱ ክብደት እና ቅለት ብቻ ሳይሆን እነሱን እንዲመሩ በተሰየመበት አከባቢዎች ጭምር ነው፡፡ ግጭቱ ቀላል ከሆነ የሁለቱም ተጋጭ ወገን አጋዴዎች ግንኙነት

በማድረግ ሌላ ሶስተኛ ወገን ሳያስፈልግ የሁለቱ ወገን አጋዴዎች ይፈታሉ፡፡ ነገር ግን ግጭቱ ከበድ ያለ እና ከሁለት አጋዴዎች ክልል በላይ ሰፊ ከሆነ የሁለቱ ወገን አጋዴዎች ሳይሆን በሌላ ሶስተኛ ወገን አደራዳሪነት ግጭቱ እንዲፈታ ይደረጋል፡፡

### 3.1.7. የጋሞ የግጭት አፈታት ስርዓት ከሀገረሰብባዊ ድራማ አላባውያን አንጻር ምን ይመስላል

የጋሞ ብሄረሰብ የራሱ የሆኑ የግጭት መፍቻ ስልት እንዳለው መረጃዎች ያሳያሉ፡፡ በግለሰቦች ይሁን በቡድኖች መካከል የሚከሰት አለመግባባቶች በውይይት መፍታትና በሰላም አብሮ ተቻችሎ መኖር ጋሞዎች ካሏቸው እሴቶች መካከል አንዱ እና ዋናው ነው፡፡ ባህላዊ የግጭት መፍቻ ዘዴዎች በአንድ ሀገር ውስጥ የመንግስት መዋቅር ተዳክሞ የሀገሪቱን አልያም የዜጎችን ሰላም እና ደህንነት ማስጠበቅ በማይችልበት ወቅት ክፍተቱን በመሙላት በየአከባቢው ሰላምና ደህንነት እንዲፈጠር የጎላ ተሳትፎ እንደሚያደርጉ ይገለጻል፡፡ ይህንን ሀሳብ በማጠናከር በጋሞ አከባቢዎች ያሉ ባህላዊ የግጭት መፍቻ ተቋም በሀገሪቱ የመንግስት ለውጥ በተደረገበት ወቅት የተፈጠረውን ክፈተት በመሙላት የአከባቢውን ሰላምና በማስጠበቅ ሂደት እንደተሳተፉ ያስረዳሉ፡፡ በጋሞ አከባቢ የሚነሱ ግጭቶችና ወንጀሎች ደረጃና ባህሪ የተለያየ ከመሆኑ የተነሳ የሚዳኙበት በተለያዩ ባህላዊ አስተዳደር እርከኖች ወይም ሸንጎዎች ነው፡፡

በጋሞ ብሄረሰብ ዘንድ አለመግባባቶች እና ግጭቶች ሲከሰቱ በአፈታት ሂደቱ ላይ የሚተላለፉት አካላት ባህላዊ አስተዳደር መሪዎች፣ ባህላዊ እምነት እናየሀይማኖት ተቋማት መሪዎች፣ ቤተሰብ፣ ጎሮቤት፣ የጎሳ መሪዎች እና የሀገር ሽማግሌዎች እንደሆኑ መሪዎች መረጃ ሰጪዎች ይገልጻሉ፡፡ ይህን ሀሳብ በማጠናከር ኬነድ (2011) ጠቅሶ የግጭት አፈታት ሂደት የሁሉኑም ባለድርሻ አካላት ተሳትፎ የሚጠይቅ ውጤቱም የሚጸድቀው በፈቃድኝነት ላይ ተመርኩዞ እንደሆነ ይገልጻል፡፡

የጋሞ የግጭት አፈታት ስነ ስርዓትን ስንመለከት በምዕራፍ ሁለት ላይ የተተነተኑት የሀገረሰባዊ አላባውያን ጋር የሚያገናኘው ነገር ቢኖር በምዕራፍ ሶስት ውስጥ የጋሞ ግጭት አፈታት ስነ ስርዓት ሲከወን በድራማዊ ድርጊያዎች ነው። (ፎክሎር ሰለሞን ተሾመ ባዬ 2007 ዓ.ም) የሀገረሰባዊ ድራማ ምንነት ላይ እንዳለው ከሆነ የሀገረሰባዊ ከዋኞች የማህበረሰቡ አባላት በመሆናቸው አብዛኞቹ ተመልካቾች የሚያውቋዋቸው እንደሆኑ በድራማዊ የሚቀርብ ታሪክም ምልልስን እና እንቅስቃሴን መሰረት በማድረግ እንደሆነ ያሳየናል። የጋሞ የግጭት አፈታት ሲከወን በድራማዊ ድርግያ በእንቅስቃሴና በንግግር ምልልስ ከዋኔውን ይፈፅማሉ። ስለዝህ ይህ የጋሞ የግጭት አፈታት ከምዕራፍ ሁለት ጋር ቅርርብ አለው። እንዲሁም ሀገረሰባዊ ሙዝቃ፣ ሀገረሰባዊ ዳንስ እና ሀገረሰባዊ ድራማንም የጋሞ የግጭት አፈታት ውስጥ ይካተታል እነዝህም የግጭት አፈታቱ ላይ ይከወናሉ።

### 3.1.8. ባህላዊ መሪዎች በግጭት አፈታት ላይ ያላቸው ሚና

በዚህ ጥናት ውስጥ ቀደም ብሎ በቀረበው ባህላዊ የፖሊቲካ መዋቅር ርዕሰ ጉዳይ ውስጥ ሁሉም የብሄረሰቡን ባህላዊ የፖሊቲካ አስተዳደር መዋቅር በዝርዝር የቀረበ ሲሆን በዚህ ክፍል ግን ከባህላዊ አስተዳድር መዋቅር ውስጥ

በብሄረሰቡ ዘንድ በቀጥታ  ግጭትን በመከላከል እና አፈታት ዙሪያ የሚሳተፉ አካላት ሚና ምን እንደሚመስል ከዚህ ቀጥሎ ተተንትኖ ቀርቧል፡፡

በጋሞ ብሄረሰብ በባህላዊ ዳኝነት ስርዓት መሰረት ካው(ካቲ) ከፍተኛው የዳኝነት አካል ስለሆነ ወደ ካዎ ችሎት የሚቀርቡ ከበድ ያሉ ግጭቶች ብቻ ናቸው፡፡ በብሄረሰቡ ዘንድ ለካዎ (ንጉስ) ከፍተኛ ስፍራ ስለሚሰጥ በካዎ የሚሰጡ ውሳኔዎች ተፈጻሚነት አላቸው፡፡ እንደ መረጃ ሰጪዎች አገላለጽ በማጋ እና በሁዱጋ የተወሰኑ ውሳኔዎች በካዎ ይጸድቃሉ፡፡

### 3.1.9. የጋሞ ግጭት አፈታት ከቃለ ተውኔት አንጻር

| **በጋሞኛ** | **በአማርኛ** |
|---|---|
| ጦሲ ኔና እንተና ጊዶ | እ/ግር ከእኛም ከእናንተ ጋር ይሁን |
| እንተና አዋን ጋጌታዲ | የት ነው የተጣላቹት? |
| አኔ ኑኒ በያንዶስ | እስኪ ደግሞ እኛ እንየው |
| አዋን አዋን ጋገቶዲ አኔ ቆርፔ | እስኪ እንፍታው |

**ግጭቱን ስጨርሱ ሚጠቀሙት ቃል**

| | |
|---|---|
| ኑና ጦስ ጋላታይ ኤኮ | እግዚአብሄር ክብሩን ይውሰድ |
| ኑኒ ጭማ ገልበይ እንተና | እኛ ሽማግሌዎች ነን ስሙን |
| ኑኒ ግግሶስ ጦሲ ጋላታይ ኤኮ | እኛ አስተካክለናል ፈጣሪ ይጨመርበት |
| ጦሲ አንጆ  ኀዲ አንጆ | እግዚአብሄር ይባርካቹ |
| ኑኒ ሳአን አቶስ | እኛ በምድር ይቅር ብለናል |
| ጦሲ ሳሎን አቶ ጎ | እግዚአብሄር በሰማይ ይቅር ይበላቹ |

### 3.1.10 የጋሞ ሀገር በቀል ከግጭት አንጻር
ግጭት ያለ እና የነበረ ነው በመሆኑም 3 አይነት ግጭቶች አሉ።

ሰው ከሰው ጋር

ሰው ከፍጣሪ ጋር

ሰው ከራሱ ጋር     አጥኝዋ የምትሰራው ሰው ከሰው ጋር ያለውን ግጭት ነው፡፡፡ ሰው ከሰው ጋር ያለውን ያለውን ክዋኔ እና በግጭቱ ውስጥ ያሉትን ስነ ስርአቶች ይዘረዘራሉ፡፡ ሰው ከሰው ጋር ሲጋጭ በምን አይነት ሁኔታና መንገድ እንደሚታረቁ በግልፅ ይቀመጣሉ፡፡ ስለዝህ የጋሞ ሀገር በቀል ግጭት አፈታት ከትውፍታዊ ተውኔት አላባውያን አንፃር በዝህ መልኩ ይገለፃል፡፡

እንዲሁም ሴራውን እንመለከታለን ሴራ ማለት የታሪክና የግጭት ድምር ሲሆን ለምሳሌ እንድ ሰው ከሌላኛው ሰው ጋር ግጭት ስፍጠር በዝያ ግጭት ውስጥ አንዱ እንዱን ለማሳመን ይሞክራል ለምሳሌ:-ውሸታም ነህ ብለው ውሸታም አለመሆኑን ለማሳመን ያ ደግሞ ውሸታም መሆኑን በሚያደርጉበት ጥረት ውዝግብ ውስጥ የድራማ እስትራክቸር የምንላቸውን እናገኛለን፡፡ እውቅያ፣ትውስብ ፣ጡዘት'፣ እናገኛቸዋለን፡፡ እነዝህ በሚሆኑበት ጊዜ ሴራው ምንድነው በግጭቱ ውስጥ ያለው ሴራ ምንድነው ሚለውን ነገር ማየት እንችላለን፡፡ ስለዝህ ሴራው ግጭቱ ጡዘት ላይ በሚደርስበት ጊዜ ያን ግጭት ለመፍታት የተጋጩበትን ምክንያት ሁሉን ነገር በዝህ አንጻር ስናየው ሴራው ምን እንደሆነ ልናውቅ እንችላለን ፡፡ ሴራ ማለት የግጭትና የታሪክ ድምር ነው፡፡ ስለዝህ ታሪኩ ሁለት ሰዎች ተጋጭተው ለመፍታት በሚያደርጉት ጥረት ሲሆን ስለዝህ በግጭት መሀል እነዝህ የድራማ እስትራክቸር ካገኘናቸው በአጠቃላይ ሴራው ታውቁዋል ማለት ነው፡፡

**3.1.11 የጋሞ ሀገር በቀል ከመቼ አንጻር**

አጠቃላይ መቼቱ አርባምንጭ ሲሆን ውስን መቼቱ ደግሞ በጨንቻ ወረዳ ዶርዜ ውስጥ ነው፡፡እንዲሁም ዱቡሻ የተባለ ዛፍ ስር ተሰባስበው ግጭቶችን ይፈታሉ፡፡ ሌላው ደግሞ ቁሳቁሶችን ጵይጠቀማሉ እንደ ጦር፣ የነብር ቆዳ፣ ከዘራ ይጠቀማሉ፡፡በተጨማሪም ከአልባሳት አንጻር ጋቢ፣ ኩታ፣ የመሳሰሉትን በመጠቀም ግጭቶችን መፍታት ይችላሉ፡፡

# ምዕራፍ አራት

## ማጠቃለያ እና የመፍትሄ ሃሳብ

### 4.1. ማጠቃለያ

በዚህ ጥናታዊ ፁሁፍ ውስጥ የጋሞ የግጭት አፈታት ምን እንደሚመስል ቱጌ የተባለው የግጭት አፈታት ምን እንደሚመስል ዱቡሻ የተባለው የግጭት አፈታት እና የሀገር ሽማግሌዎች እንዴት አድርገው ግጭቱን እንደሚፈቱ ግጭቶች በምን ምክንያት እንደሚነሱ የሀገር ሽማግሌዎች በግጭቱ ላይ ያላቸው ሚና ምን እንደሚመስል ተዘርዝረዋል።

- ✓ የጋሞ የግጭት አፈታት ሪሰርች ከሀገረሰባዊ አላባውያን አንፃር ሀሳብ ማንሳት
- ✓ ከሀገረሰባዊ ድራማ ድርግያ አንፃር በመተንተን

እንዲሁም የግጭት አፈታቱ ሲፈፀም ምን አይነት ዝግጅቶች እንደሚደረጉ በግልፅ ተቀምጧል። በተጨማሪም የሀገረሰባዊ ድራማ ምንነት የሀገረሰባዊ ትውን ጥበብ የሀገረሰባዊ ዳንስ፣ የሀገረ ሰባዊ ሙዝቃ ምን እንደሚመስል በመተንተን በዝርዝር ተቀምጠዋል።

ይህን ሁሉ መረጃዎች አሰባስቦ በአጠቃላይ ይህ የጋሞ የግጭት አፈታት ከሀገረሰባዊ ድራማ አላባውያን ጋር አንድነት እንዳለው ሙዚቃ ከሙዚቃው ጋር እንቅስቃሴው ከእንቅስቃሴው ጋር ቃለ ተውኔቱ ከድራማ ድርጊያው ጋር አንድነት እንዳላቸው አረጋግጣለች፡፡ ምክንያቱም የግጭት አፈታቱ ሲከወን ተመሳሳይነት አለው። ከድራማ አላባውያን አንፃር እነዚህን በማጤን ከዚህ ሀገረሰባዊ ድርጊያ ጋር አንድነት እንዳለው አረጋግጣለች።

### 4.2. የመፍትሄ ሀሳብ

ከላይ በማጠቃለያ እንደተገለፀው አጥኚዋ በጥናቱ ወቅት የተገነዘበችው ችግሮች እና ጥናቱን ለመስራት አነሳሽ ምክንያት እንደ ችግር ተነስተዋል። ስለዚህ የጋሞ የግጭት አፈታት እየተመረዘ፣ እየተረሳ፣ እንደሆነ መገንዘብዋን ገልጻለች። እናም ይህንን ለማስቆም ወይም ለመታደግ ለማስታወስ፣ ባህሎች በሀገረሰባዊ ድራማ ቢጠኑ ወደ መድረክ ቢወጡ ቢመደረኩ ባህልን መታደግ እንችላለን። እንዲሁም በተለያዩ የጥበብ ዘውጎች ቢጠኑ እና ለመድረክ ቢበቁ ሙሉ በሙሉ ማስታወስ ይቻላል።

- ✓ ጸሐፊዎች ወይም ሪሰርቸሮች እንደዚህ አይነት ክንውን ላይ ትኩረት እንዲያደርጉ

- ✓ የሀገር ሀብት ስለሆነ እንደዚህ አይነት ነገሮች እንዳይጠፉ ጸሐፊዎች ትኩረት ቢሰጡ ጥሩ ነው።
- ✓ መረጃ ለመሰብሰብ በሄድኩበት ጊዜ መረጃ ሰጪዎች ባለመኖራቸው ሌላ ሰዎችን በመጠቀም

**ታካይ ክፍል**

ቱጌ.......................................................................................................ጦር

ዱቢሻ.....................................................................................................እርቅ ሚፈጸምበት ስፍራ

አጋዴ.....................................................................................................መንገደኛ

ካዎ......................................................................................................ንጉስ

ማጋ......................................................................................................እርቅ ፈፃሚ

ሁዱጋ...................................................................................................እርቅ ፈፃሚ

ጭማ.................................................................................................... ሽማግሌ

ኡሎ አላ................................................................................................የጩሁት አይነት

ጎሜ......................................................................................................እርግማን

ጎምፓ....................................................................................................ከእርቅ በሁዋላ የሙብል ፕሮግራም መፈፀም

ዮ.... ዮ.... ዮ........................................................................................ እርቅ አውርደናል

ኢጋሳ.................................................................................................... ግጭትን የማርገብ ስራ የሚሰሩ

ጋና...................................................................................................... የእድሜ ባለፀጋ

## ዋቢ መጽሀፍት


ሰለሞን ተሾመ ባዬ ፡፡ _ፎክሎር_፡፡ አዲስ አበባ፤ ፋር ኢሲት ትሬዲንግ.ኃላ.የተ.የግ. ማ ፣2007፡፡

በጋሞ ጎፋ ዞን ማስታወቂያ እና ባህል መምሪያ ታህሳስ 2001 ዓ.ም አርባምንጭ

በደ.ብ.ብ.ሕ ክልላዊ መንግስት የብሄረሰቦች ምክር ቤት፣ አርባ ምንጭ ዩኒቨርሲቲ እና የጋሞ ጎፋ ዞን ባህልና ቱሪዝም የመንግስት ከሙኒኬሽን መምሪያ ሐዋሳ ግንቦት 2008 ዓ.ም

አለም እሸቱ: _መሰረታውያን የምርምር የዘገባ ዘዴ_ (1994÷148)

የአዲስ አበባ ከተማ የጋሞ ልማት ማህበር ማስተባበሪያ የ 2012 ዓ.ም የባህል ቋንቋ ሲምፓዚየም ንቅናቄ የተዘጋጀ የካቲት 30 2012 ዓ.ም

የጋሞ ጎፋ ባህልና ቱርዝም መንግስት ኮምንኬሽን መምሪያ (2008) ፡፡ የአምስቱም ብሄረሰብ አፋዊ ትዉፍት አርባምንጭ ኤፍ ቢ ደብሊዉ ማተሚያ

ዘሪሁን አስፋዉ (1996) ፡፡ የስነ-ቃል መሰረታዊ አዲሲ ንግድ ማተሚያ

ጌታቸዉ በለጠ (2004) ፡፡ የጥበብ ጉባኤ አዲሲ አበባ አስቴር ነጋ አሳታሚ ድርግት

ፈቃደ አዘዘ (1991) ፡፡ የስነ-ቃል መምሪያ አዲሲ አበባ ቦለ ማተምያ ድርጅት (505)992-76001 askus folk art (------), folk art market organ

## አባሪዎች

አባሪ አንድ፡ ለቃለ መጠየቅ የተዘጋጁ ጥያቄዎች

1. የጋሞ ብሄረሰብ የግጭት አፈታት ክዋኔ ምን ይመስላል?
2. የጋሞ አባቶች ባህሉ ላይ ያለውን የግጭት አፈታት ስነ ስርዓት ያላቸው ሚና ምን ይመስላል?